# Envision Cambridge

## ማጠቃለያ ሃሳብ



ለካምብሪጅ ከተማ የማህበረሰብ ልማት ክፍል የተዘጋጀ
ይህ ሠነድ የካምብሪጅን ራዕይ የአተገባበር ዕቅድ ሂደትን
በማሳጠር የቀረበ ማጠቃለያ ሠነድ ነው፡፡
ሙሉ ዕቅዱን ለማግኘት እባክዎ envision.cambridgema.gov

ድረ ገጽን ይጎብኙ።

## ዋናው ቢሮ(Executive Office)

Louis A. DePasquale,የከተማው ሥራ አስኪያጅ
Lisa C. Peterson,የከተማው ምክትል ሥራ አስኪያጅ

## የከተማው ምክር ቤት(City Council)

Marc C. McGovern,ከንቲባ
Jan Devereux,ምክትል ከንቲባ
Dennis J. Carlone
Craig A. Kelley
Alanna M. Mallon
Sumbul Siddiqui
E. Denise Simmons
Timothy J. Toomey, Jr.
Quinton Y. Zondervan

## የዕቅዱ ቦርድ አባላት (Planning Board)

H. Theodore Cohen, ሊቀመንበር
Catherine Preston Connolly, ምክትል ሊቀመንበር
Louis J. Bacci, Jr.
Nikolas Bowie
Steven A. Cohen
Corinne Espinoza
Mary T. Flynn
Hugh Russell
Tom Sieniewicz

የዚህን ፕሮጀክት ማዕከል ለማግኘትና ሙሉ የሠራተኞቹን አባላት

እንዲሁም የማህበረሰቡ ደጋፊዎችና አስተዋጽኦ አድራጊዎችን ዝርዝር ለማየት

ከገጽ 26-29 ይመልከቱ


S4MS



# የ2030 ዕቅድ

የካምብሪጅ ራዕይ-የካምብሪጅ ከተማ አጠቃላይ ዕቅድ ሲሆን ከተማዋ የተሻለ ፣ዘላቂ፣ እኩልነት የሰፈነባት እና አካታች ማህበረሰብን የሚፈጠርባት ከተማ እንድትሆን የተዘጋጀ ዕቅድ ነው፡፡ ይህ ዕቅድ በቀጣይ ዓመታት ላቅ ያሉ ነገር ግን ሊሳኩ የሚችሉ ግቦችን ለማሳካት ስልቶችን ያስቀምጣል፡፡

በማህበረሰቡና ለማህበረሰቡ የተቋቋመ በመሆኑ የካምብሪጅ ራዕይ ጫና እየፈጠሩ ላሉ የከተማ ተግዳሮቶች መፍትሄ ለማስገኘትና ካምብሪጅን ለመኖር፣ ለመስራትና ለጉብኝት አመቺ የሆነች ቦታ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማሳደግ የካምብሪጅ ራዕይ የከተማዋን ጠንካራ ጎኖች- ህዝቡን ፣ ንግዶችን እና ተቋማትን ፣የፈጠራ ታሪክንና ተራማጅ እሴቶችን ይጠቀማል፡፡

ባለፉት ሶስት ዓመታት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በአካታች የህዝብ የስራ ሂደት አማካይነት በካምብሪጅ ራዕይ ልክ ቅርፅ እንድትይዝ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በጋራ በመስራት እንደማህበረሰብ ቁልፍ የሆኑ እሴቶቻችንን ለይተናል፡፡ እንዲሁም የአየር ንብረትና አካባቢ፣ የማህበረሰብ ደህንነት፣ ኢኮኖሚ፣ የቤት ተደራሽነት፣የመጓጓዣ (ትራንስፖርት) እና የከተማ ቅርፅ በሚሉ በስድስት የዕቅድ አወጣጥ ርዕስቶች ስር ለከተማዋ የወደፊት ዕጣፈንታ የጋራ ራዕይን አስቀምጠናል፡፡ ዕቅዱ ራዕዩን ለማሳካት 37 መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ደግሞ ለፖሊሲዎች፣ መርሃግብሮች ፣የዞን ለውጦች፣ ማህበረሰብን መድረስ እና ትምህርት፣ የካፒታል ኢንቨስትመንት እና በመንግስትና በክልል ደረጃ የሚከናወኑ ለዚሁ አላማ በመቆም የመሚገት ጥረቶችን ያካትታል፡፡ እያንዳንዱ የቀረበ የመፍትሄ ሀሳብ ህያው ለማድረግ በሚመጡት ዓመታት ተጨማሪ ስራ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ እርምጃዎች ተጨማሪ ትንተና ፣ ጉልህ የሆነ የመንቀሳቀሻና የካፒታል ገንዘብ እና/ወይም ቀጣይነት ያለው የማህበረሰብ ተሳትፎ ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ መሰረት የካምብሪጅ ራዕይ ለትግበራ የሚቀል አሰራርን ተከትሎ በተለያዩ ሎጂስቲካዊ ፣ ገንዘብ እና ቴክኒካል ፍላጎቶች እንዲሁም በጊዜው ውስጥ በሚለወጡ ሌሎች ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ አድርጎ ለማበረሰቡ ዕድልና እውቅና ይሰጣል፡፡ የትግበራው ጊዜ የዕቅዱን ግቦችና ራዕይ ለማሳካት በወቅቱና የካምብሪጅ ራዕይ ህያው ሰነድ ሲሆን በጊዜው ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ለውጦችንና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተለዋዋጭ ጉዳዮችን ለማስተናገድ በየጊዜው መሻሻል ይደረጋል፡፡ የስራ ሂደት ክንውን መሻሻልን ባለማቋረጥ በመለካት እናሳውቃለን፡፡ ዕቅዱ ለውጥን ለመደገፍና የማይለዋወጥ መመሪያ ሆኖ እንዲቀጥል የተለያዩ ማሻሻያዎችን የሚያደርግ ሲሆን ከነዚህም፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶች እንዲኖሩ ለማድረግ ፣ ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማሳደግ ፣ ውጤታማ የመጓጓዣ አማራጮችን ለማቅረብ ፣ የአካባቢ ዘላቂነትንና እንደገና ማቆጥቆጥን ለማሳደግና የወደፊቱ ትውልድ የሚደሰትበትን የሚጎመራ እና አካታች የሆነ

ግቦችን ፣ 42 ስልቶችን እና 175 አዲስ ወይም የተሻሻሉ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎችን አቅርቧል፡፡

ለወደፊቱ እንዲኖር በታቀደው የከተማ በጀት ፣የማህበረሰብ ግብዓት እና አስተዋፅዖ ላይ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ማህበረሰብን ለማሳደግ የሚጠቅሙ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን ለመምራት እንዲችል የማይለዋወጥ ሆኖ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡

envisioncambridgema.gov

# ራዕይ እና ቁልፍ የሆኑ እሴቶች

የካምብሪጅ ራዕይ ቡድን ከማህበረሰቡ ጋር በአውደ ጥናቶች ፣ አንድ ለአንድ በተደረጉ ውይይቶች ፣ በዳሰሳ ጥናቶች እና በበለጠ ሁኔታ ደግሞ ለከተማዋ የራዕይ መግለጫን ለማስቀመጥ ሰርቷል፡፡

መጠነ ሰፊ የሆነ ማህበረሰብን የመድረስ ስራ ከተከናወነ በኋላ ዕቅዱ በካምብሪጅ ማህበረሰብ የሚገለፁ የዕቅድ ግቦችንና የመፍትሄ ሀሳቦችን ቅርፅ የሚያስይዙ ስድስት ዋና ዋና እሴቶችን ለይቶ አስቀምጧል፡፡ ራዕዩና ቁልፍ እሴቶች በአንድ ላይ የካምብሪጅ ለውጥ መሰረት የሚያደርጋቸውን የዕቅዱ የመፍትሄ ሀሳቦች ላይ መሰረትን ይጥላሉ፡፡

*“ካምብሪጅ ወደፊት መገሰገስን የምታስብ፣ ሌሎችን የምትቀበልና ልዩነትን የምታስተናግድ ከተማ ናት፡፡ ከፍተኛ ጥራት ያለው ህይወት ስለምንደሰት ዘላቂነት ባለው፣ አካታች በሆነና እርስ በርሱ በተገናኘ ማህበረሰብ እንኖራለን”*

## ራዕይ

## ዋና ዋና እሴቶች

### ህይወትን የተላበሰ መሆን

በንቃት የተሞላ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ የሆነ አካባቢን ዋጋ እንሰጣለን፡፡ እንዲሁም ተመጣጣኝ እና አመቺ የሆነ በየቀኑ ወደፍላጎቶቻችን እና የመዝናኛ ስፍራዎች ለመድረስ የሚያስችል ዘላቂነት ያለው መጓጓዣ እንደግፋለን፡፡

### ልዩነትና እኩልነት

ልዩነታችንንየምናደንቅና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው የቤት አማራጮችና ዕድሎች እንዲኖሩ ለማድረግ የምንሰራ ሌሎችን የምንቀበል ማህበረሰብ ነን፡፡

### ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች

የነዋሪዎችን ኢኮኖሚያዊ ዋስትና የሚደግፉ ጥራት ያላቸው ስራዎች ፣ የሰራተኛ ልማት ፣ ስልጠናና ማራኪ ክፍያዎች በማቅረብ ዕድልና መረጋጋትን እንፈጥራለን፡፡

### ዘላቂነትና አይገበሬነት

በአካባቢ ላይ ያለንን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስና አይገበሬ ከተማና ጠንካራ ማህበረሰብ ለመገንባት ኃላፊነትን የተላበሰ እርምጃ እንወስዳለን፡፡

### የማህበረሰብ ጤንነትና ደህንነት

ከጎረቤቶቻችንና ተፈጥሮ ጋር ለመገናኘት እንዲሁም በማህበረሰብ ህይወት ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን የተለያዩ ዕድሎች ባሉበት ደጋፊ ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ ውስጥ ጤናማና ንቁ የአኗኗር ዘይቤን እናሳድጋለን፡፡

### መማር

በህይወት ዘመን ሁሉ መማርህ እንደግፋለን፡፡ እንዲሁም በባህል በበለፀገ ማህበረሰባችን ውስጥ ስነ-ጥበብና ፈጠራን እናደንቃለን፡፡

# በዚህ ዕቅድ ውስጥ የተካተቱ ቁልፍ ጉዳዮች

1. **እያደገ ያለ ኢኮኖሚና ለዋና ዋና ኢንዱስትሪዎች ለውጥ**

በአሁኑ ወቅት በካምብሪጅ ውስጥ ካሉ ስራዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በትምህርት ወይም በሙያዊ እና ቴክኒካዊ አገልግሎቶች ላይ የተመሰረቱ ሲሆኑ ይህም የህይወት ሳይንሶችና የቴክኖሎጂ ኢንዲስትሪዎችን የሚያካትት ነው፡፡ሌላው በዋናነት መካከለኛ ገቢ ክፍያን የሚያስገኙ የኢንዱስትሪ ስራዎች በጊዜው ውስጥ ቀንሰዋል፡፡

2. **የሕዝብ ቁጥር መጨመር**

የካምብሪጅ ህዝብ በፍጥነት እየጨመረ ያለ ህዝብ ነው፡፡ በወቅቱ አዝማሚያዎች የከተማዋ የህዝብ ብዛት በ2030 እንደገና በ1950 የነበራትን ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር 120,000 የሚጠጋ ለመሆን በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡

3. **እየጨመረ ያለ የኑሮ ደረጃ ልዩነት፡-**

ምርታማ የሆነ ኢኮኖሚ ቢኖረንም ሁሉም በዕድገቱ ጥቅሞችእየተጋራ አይደለም፡፡ በደመወዝ ዕድገት፣ በትምህርት ዝግጅት ፣ በቤት ባለቤትነትና ሌሎች ጉዳዮች በተለያዩ ዘሮች ፣ ብሄሮችና የኑሮ ደረጃ ባላቸው ግለሰቦች መካከል ጉልህ የሆኑ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡

4. **ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶች እየቀነሱ መምጣት፡-**

የቤት ጥያቄ እየጨመረ መምጣቱ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ቁጥር እንዲቀንስ እያደረገ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ለንግድ ቢሮ/ቦታ ያለው ጥያቄ ከፍተኛ መሆኑ ደግሞ የቤት ኪራይ ዋጋ እንዲጨምር አድርጓል እንዲሁም ትላልቅ፣ ባለፀጋ ድርጅቶች ለሪል ስቴት መክፈል የሚችሉ ትናንሽ ንግዶችን፣ በአካባቢው ነዋሪዎች የተጀመሩ ጥቃቅን ንግዶችና ትናንሽ ተከራዮችን እያስለቀቁ ነው፡፡

5. **ተለዋዋጭ የአየር ንብረት**

እየጨመረ ያለ የሙቀት መጠንና በጣም እየተደጋገመ ያለና በከፍተኛ ደረጃ ተለዋዋጭ ሆነ የአየር ሁኔታ የጎርፍ ስጋቶችና ከመጠን በላይ ከፍ ያለ ሙቀት ክስተቶችን እንዲጨምሩ እያደረገ ነው፡፡ በ2070 እነዚህ ስጋቶች አስደናቂ በሆነ መልኩ ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡

6. **የስራ ባህሪ ተለዋዋጭነት**

መረጃ መር የሆነ ኢኮኖሚ ከተሻሻለ የቢሮ ስራ አውቶሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር ተጨምሮ እየጎለበቱ ያሉ የስራ ቦታ ኮምኒኬሽን ሲስተሞችና ዲዛይን አዝማሚያዎች፤ለተለያየ ጥቅም የሚውል ግንባታ፣ ማዕከላዊ የመገናኛ ስፍራወችና መልካም ትራንስፖርት ፍላጎትን ፈጥረዋል፡፡ በተጨማሪም የኤሌክትሮኒክ ንግድ (ኢ-ኮሜርስ) መፈጠር የችርቻሮ ንግድ ባህሪን እየለወጠው ነው፡፡ በቅርብ

7. **ለውጥን ማስተናገድ**

የማጓጓዣ ስርዓቶችንና በፍጥነት እየተቀየሩ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን የማቀናጀት አዲስ የሆነ ዘዴ በከተማችንና በክልላችን የምንጓጓዝበት መንገዶች ላይ መሰረታዊ ለውጥን እንደሚያመጣ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አሁን ያሉንን ዘላቂ የማጓጓዣ አማራጮችን ለማጠናከር ብዙ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

8. **ተለዋዋጭ የከተማ ቅርፅ**

የኢኮኖሚ፣ የማህበረሰብ ፣የህዝብ ቁጥርና አካባቢ ለውጦች በእነዚህ የዕቅድ አወጣጥ ስራዎች ጠቅለል ተደርገው የተገለፁት ከተማዋን ሊተነበይ ወደሚችል መፃኢ ዕድል በፍጥነት በተጨባጭ ሁኔታ እንደገና እንድታድግ ለማድረግ መልካም ተፅዕኖ ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ዓመታት የየቀኑ የየብስ ማጓጓዣና የዕቃ አስረካቢ ተሽከርካሪዎች መጠን በከተማይቱ ጎዳናዎች ላይ ጉልህ በሆነ መልኩ ጨምረዋል፡፡

envisioncambridgema.gov

# የአተገባበር ሂደት ጥቅል ሃሳብ

በአተገባበር ሂደቱ የመጀመሪያ ደረጃ የካምብሪጅ ራዕይ ቁልፍ የሆኑ ችግሮችንና ዕድሎችን ለመለየት፣ የከተማ አቀፍ ራዕይን ለማጎልበት እና የእኛን ዋና ዋና እሴቶች ለማስቀመጥ የማህበረሰብ ግብዓትና የመረጃ ትንተናን ተጠቅመዋል፡፡ የእኛ ራዕይና ዋና ዋና እሴቶች በስድስቱ የዕቅድ አወጣጥ ርዕስቶች :- የአየር ንብረትና አካባቢ፣ የማህበረሰብ ደህንነት ፣ ኢኮኖሚ ፣ የቤት ተደራሽነት፣ ለውጥን ማስተናገድና የከተማ ቅርፅ ዙሪያ ለዕቅዱና ምሪት የሚሰጡ የመፍትሄ ሀሳቦች እንደመሰረት በመሆን አገልግለዋል፡፡

በሁለተኛው ደረጃ በዕቅድ አወጣጥ እርዕሶች ላይ በጥልቀት እየሰራንባቸው ነው፡፡ ረቂቅ ግቦችም ፣ስልቶችንና

ለእያንዳንዱ ርዕስ የድርጊት መርሃግብሮችን ለማዘጋጀት ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩ የስራ ቡድኖችን ፈጥረናል፡፡ እንዲሁም የማህበረሰብ ግብዓትን ተጠቅመናል፡፡ በመጨረሻም




እያንዳንዱን ግብ ለማሳካት የሚደረገውን

የስራ ሂደት መሻሻል ለመከታተል ሊለኩ የሚችሉ ጠቋሚዎችንና ግቦችን አጎልብተናል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ግቦች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ለመረዳት፣ በእያንዳንዱ የዕቅድ አወጣጥ የመፍትሄ ሀሳቦችን ሚዛናቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግና የጋራ ቅድሚያ የሚሰጣቸው

ጉዳዮችን በግልፅ ለማስቀመጥ የማህበረሰብ ውይይቶችን አድርገናል፡፡

ግንኙነቶችን ለመረዳት፣ በእያንዳንዱ የዕቅድ አወጣጥ የመፍትሄ ሀሳቦችን

ሚዛናቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግና የጋራ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን በግልፅ ለማስቀመጥ የማህበረሰብ ውይይቶችን አድርገናል፡፡

## በመተባበር መንፈስ መስራት

ሶስት ዓመት በፈጀው ከህዝብ ጋር የተከናወነ የስራ ሂደት በሺዎች የሚቆጠሩ የማህበረሰብ አባላት የካምብሪጅ ራዕይን ቅርፅ እንዲይዝ አድርገውታል፡፡ የማህበረሰብ ተሳትፎ በትክክል የማህበረሰቡን የወደፊት ፍላጎቶች የሚገልፅ ትክክለኛ የሆነ ትርጉም ያለው የረጅም ጊዜ ዕቅድን ለማውጣት አስፈላጊ ነበር፡፡

ዲዛይኑ ሁሉም ማህበረሰብ ሃሳብ እንዲለዋወጥ አመቺ የሆነ መድረክ ፈጥሮላቸዋል፡፡ውይይቱ ለሁሉም አሳታፊ እንዲሆን ከተማው በርካታ ሰዎችን ይደርሳል፡፡

የሚከተሉት አሳታፊ ዓላማዎች ይህን የመድረስ ሂደትብ ይመራል፡፡

የCambridge ከተማ

- . ስ/ ዕውቀትና ልምድ ይሰበስባል፤ግብዓት ይቀበላል፡፡
- በማህበረሰቡ አባላት መካከል ስለሂደቱ መግባባት እንዲዳብርና የተለያዩ ዕይታዎች እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡
- አካታችነትና መጠነ ሰፊ የሆነ ህዝባዊ ስራ ለመስራት

ማህበረሰባዊ አካታች መድረክ ይፈጥራል፡፡

- የሁሉም ህብረተሰብና አጋሮች የጋራ ራዕይ ተጠቅሞ ለከተማው የወደፊት መጻኢ ልማት ያዘጋጃል፡፡

- ለቀጣይ ትብብር፤ተሳትፎና ህብረተሰብ የመድረስ ስራ ይሰራል፡፡

ዓላማዎቹን ለማሳካት ሰዎችን በአካል፤በኢሜይልና የተለያዩ የኦንላይን መሳሪያዎች በመጠቀም ህብረተሰቡን አሳታፊ ያደርጋል፡፡እነዚህም

- ሰባት የነዋሪዎች፤የነጋዴዎችና ተቋማዊ አጋሮችን ያካተተ ኮሚቴ

- ህዝባዊ ዎርክሾፖች፤ክፍት ቤቶችና ፓናል ውይይቶች

- ከማህበረሰቡ አሳታፊ ቡድን ጋር በመተባበር በካምብሪጅ ውስጥ ተጠቃሚ ያልሆኑ አሜሪካ የተወለዱ ጥቁሮችን፤ባንግላዴሻዊያን ፤ቻይናዊያን፤ኢትዮጵያዊያ ን፤ሐይቲያዊያንና ስፔናዊያን እንዲሁም አረብኛ ተናጋሪ ማህበረሰቦች

- የአካባቢውን ትዕይንቶች፤ፌስቲቫሎች፤መና ፈሻዎች፤የገበሬዎች ገበያ፤ቤተመጽሐፍቶች፤ከፍተ ኛ የቤትና ሌሎች የጎረቤት አካባቢዎች የጎበኙ የጎዳና ቡድኖች

- ለወደፊት ልማት ጠቃሚ የሆኑ ተንቀሳቃሽ አሳታፊ ጣቢያዎች፤ጎዳናዎችና እንቅስቃሴዎች

- በማሳቹሴት እና ካምብሪጅ ጎዳናዎች የእግር ጉዞ ማድረግ

- በየኦንላይን እና በወረቅት አማካይነት የሚደረጉ ጥናቶች

- በጋዜጣ ላይ የሚወጡ ካርታዎች፤ዳታ ፤ታሪክ ፤አስቂኝ እውነቶች ፤ህዝባዊ ዕውቅና ያላቸው ምስሎችና ቃለ መጠይቆች ከማህረበሰቡ አባላት ጋር በመተባበር ማዘጋጀት

- ዲጂታል የሆኑ መሳሪዎች ፤የማህበረሰቡ አባላት ኦንላይን በቀን 24 ሰዓት በሳምንት 7 ቀናት ስለግቦቹ ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ ፤አስተያየታቸውን እንዲሰጡና ከሌሎች ተጠቃሚዎች ጋር እንዲገናኙ ማድረግ ናቸው፡፡











# ክንውኖች በቁጥር ሲገለፁ

5,000 115

በጎዳና ቡድናችን ያገኛቸው ተሳታፊዎች ብዛት በሠባት ኮሚቴዎችና የስራ ቡድኖች ውስጥ የሚገኙ የኮሚቴ አባላት ቁጥር

2,000 165

የኦንላይንና በአካል ጥናት የተሰጡ ምላሾች ብዛት የኮሚቴና የስራ ቡድን ስብሰባዎች የወሰዱት ሰዓታት

5,000160

የማህበራዊ ሚዲያ ትስስር ብዛት ድምጻቸው ያልተሰሙ ማህበረሰቦች ውስጥ የተመረጡ ተሳታፊዎች ቁጥር

50074

የሕዝብ ዎርክሾፕ ተሳታፊዎች ቁጥር ዎርክሾፕ፤ፓናሎችና የስራ ቡድን ስብሰባዎችን ያካተቱ የሕዝባዊ ስብሰባዎች ቁጥር

# አሁን ያለው የወረዳው አቀማመጥ



በጎረቤት አቅራቢያ የሚገኙ የነዋሪ መንደሮ

መስቀለኛ ጎዳናዎችና ዋና ዋና የተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ኮሪደሮች

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙባቸው አካባቢዎች

መሸጋገሪያ ቦታዎች

ብቅ እያሉ ያሉ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ወረዳዎች

**ይህ ምስል የከተማውን የተለያዩ ክፍሎችን በከፊል የሚገለጽ ሲሆን ዲዛይኑ የተሰራው አሁን ያለውን ሁኔታና ወደፊት ሊኖር የሚችለው ግምታዊ ለውጦችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡**

# የመፍትሄ ሀሳቦች

## ዕድገትን መቆጣጠር

የካምብሪጅ ታሪክ የለውጥ ታሪክ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ላለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት ለለውጥ ያለው ጫና ጨምሯል፡፡ ጠንካራ ኢኮኖሚያችን፣ ታዋቂ ዩኒቨርስቲዎቻችን፣ ማራኪ የከተማ መሰረታዊ አገልግሎት መስጫዎቻችን፣ ታላቅ የመዘጋጃ ቤት አገልግሎታችንና ከፍተኛ ጥራት ያለው ህይወት ከተማችንን ለኑሮ ፣ለስራ፣ ለትምህርትና መዝናናት በክልላዊና በብሄራዊ ደረጃ እጅግ በጣም ከሚፈለጉ ከተማዎች ውስጥ አንዷ አደርጓታል፡፡ የካምብሪጅ ተነፃፃሪ ጥቅምና ምቾትን የሚፈጥሩ ተቋማት ለቦታ ያለ ፍላጎት ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡ ከዚህ የተነሳ በከተማው ውስጥ አዳዲስ ልማቶች/ግንባታዎች እንዲከናወኑ ያደረገ ሲሆን ማህበረሰቡም ከህዝብ ብዛት ፣ ኢኮኖሚያዊና ፊዚካላዊ ለውጦች የተነሳ ጫናዎችና ውጥረቶች እየተሰሙት ይገኛል፡፡

የካምብሪጅ ራዕይ አሁን ባሉ ልማቶች ላይ የተመሰረተና አሚይ የሆነ የዕድገት ቁጥጥር ማዕቀፍን አስቀምጧል፡፡ የአሁኑን ማህበረሰብና የወደፊቱን ትውልድ ፍላጎቶች እያሟላ ለከተማዋና ሰፈሮቻችን ልዩ ባህሪ ዕድገትን ለመቆጣጠር የመጀመሪያውን እርምጃ የተለያዩ የካምብሪጅ አውራጃዎችንና ሰፈሮችን መመዝገብ ነው፡፡ ካምብሪጅ ብዙ ታሪክ ያላት ውስብስብ ስፍራና የዕድገት ጫናዎቿም የማንኛውም በውስጧ የሚገኝ ስፍራ የወቅቱ ገፅታ ላይ ተፅዕኖ እያደረገ የሚገኝባት ናት፡፡ ይህንን ካልን የሚከተለው ዝርዝር አሁን ያሉትን ሁኔታዎች ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል፡፡ እንዲሁም ለወደፊቱ ዕድገት ያለ አቅምን ይገልፃል፡፡

### የመኖሪያ ሰፈሮች:

ዝቅተኛ ዕድገት የሚጠበቅባቸው ፣አሚይ የሆነ ዕድገትን እያሳዩ አሁን ያለውን መዋቅራቸውን አብዝተው የሚጠብቁ ፣ ከሰፊው የከተማዋ ግቦች ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡ ብዙ የተለያዩ ፣ ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ ግንባታዎች ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ የማጓጓዣ ጥጎች(ኮሪደሮች) ዙሪያ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

### አደባባዮችና ዋና ዋና የተለያየ ጥቅም የሚውሉ ጥጎች

በማሳቹሴት ጎዳናና ካምብሪጅ መንገድ ላይ የሚገኙ የማጓጓዣ ቅርበትን የሚጠቀምና ልዩ ባህሪያቸውንና የቦታ ሁኔታቸውን ሊያሳድግ በሚችል መልኩ በመካከለኛ ፣ በተለካ ፍጥነት ማደግ ይኖርባቸዋል፡፡

### የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካባቢዎች

በመጀመሪያ ደረጃ በተለመዱ ዋና ግቢዎቻቸው ውስጥ እንዲያድጉ ሊደረጉ ይገባል እንዲሁም ከተለመዱ የመኖሪያ አካባቢዎች ጎን ሳይርቁ ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ ግንባታዎች ጎን ሌላ ተጨማሪ ግቢ መገንባት ይችላሉ፡፡

### የሽግግር አካባቢዎች

ጎን ለጎን በሚከናወኑ ተግባራት መካከል መካከለኛ ስኬል የሚፈጥሩ የተለያየ ዓይነት ግንባታዎችን/ ልማቶችን ሊያስተናግዱና በቅርበት ያለ የመሬት አጠቃቀም ጥቅሞች ላይ ትኩረትን የሚሰጡ ልማቶችን ማስተናገድ አለባቸው፡፡

### እያደጉ ያሉ ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ ግንባታዎች የሚከናወኑባቸው አውራጃዎች

ኬንዳል አደባባይ፣ ኖርዝ ፖይንት/ ካምብሪጅ ክሮሲንግና አለዋይፍ የከተማዋ ዕድገትና ለውጥ የመጓጓዣ ቅርበት ዕድልን በመጠቀምና በመሬት ላይ የመኪና ማቆሚያ ፣ በቤት መኪና ላይ ያተኮረ አጠቃቀምና ባረጁ የንግድ ህንፃዎችን የሚታወቁትን አካባቢዎች በመልካም ሁኔታ በመለወጥ የከተማዋን ከፍተኛ ዕድገትና ለውጥ ማስተናገዳቸውን ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

የሚሰጠውን ታሪክ መጠበቅ ይፈልጋል።

envisioncambridgema.gov

# የአየር ንብረትና አካባቢ

ካምብሪጅ ጥቅጥቅ ያለች፣ መጓጓዣ ጭረት ተኮር ከተማ ስትሆን ቀጣይነት ያለው እያደገ የሚሄድ አካባቢያዊ ባህልና የተጋነነ አካባቢያዊ ዕቅድ አወጣጥ እየተከናወነበት ያለች ከተማ ናት ከተማዋ ለሁሉም የሚጠቅም የአካባቢ ደህንነትን ለማሻሻልና በአየር ንብረት ላይ እና በክልላዊ የአካባቢ ስርዓት ላይ ያላትን አሉታዊ ተፅህኖ ለመቀነስ በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡ ክልላዊ ከኢንዱስትሪ ነጻ የማድረግ ስራ በተከናወነበት፣ ለአካባቢያዊ ችግሮች ዕውቅና መስጠት ባደገበትና በአካባቢያዊ መንግስት የተቀናጀ እርምጃ በተወሰደባቸው አስርት ዓመታት የካምብሪጅ አፈር ፣አየር፣ ውሃና ፍሳሽ መተላለፊያ ተሻሽሏል፡፡ ቢሆንም የዓለምአቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ የበለጠ ጉልህ እየሆነ በመምጣቱ እየጨመረ ያለውን የጎርፍና የከባድ ሙቀት ስጋትንም ጭምር ልንዋጋ ይገባል፡፡ እነዚህ ስጋቶች ደግሞ የመነጩት እየተለወጠ ካለው ቁስ አካላዊ አካባቢ ነው፡፡ ነገር ግን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በአየር ንብረት ለውጥ እጅግ ተፅዕኖ የደረሰበት ላይ አሉታዊ ውጤትን ያስከትላሉ፡፡ ካምብሪጅ ለእነዚህ የተለያዩ ችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ስራዋን ብትቀጥልም ያረጁ የመሰረተ ልማት አውታሮች፣ እንደ ኢኮኖሚያዊ ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖች የማትበገር ዘላቂ ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ በኃይል አጠቃቀም፣ የተፈጥሮን አካባቢን ባለአደራ ሆኖ በመንከባከብ ፣ ከባድ የሆነ የአየር ፀባይ አሉታዊ ውጤትን በመቀነስ እና የነዋሪዎቿ ጤንነትና ደህንነት መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ትገነዘባለች፡፡

## ግቦች

**የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ የሚወሰድ እርምጃ፡-** በ2050 ከካርቦን ልቀት ነፃ መሆን

**ለአየር ንብረት ለውጥ ዝግጁነት፡-** የካምብሪጅ ማህበረሰብን ህይወትና ኑሮ ከአየር ንብረት ለውጥ መታደግ

**የአካባቢ ጥበቃ፡-** የካምብሪጅን ብዝሃ ህይወት፣ ክፍት ቦታዎችና መኖሪያ አካባቢዎችን መጠበቅና ማሳደግ

**የውሃ ጥራት** ፡- ዘላቂነት ያለውን የውሃ ሀብቶችን መጠበቅና የውሃ ጥራትን ከፍ ማድረግ

**የቆሻሻ አያያዝ፡-** ቆሻሻ ማመንጨትን መቀነስና በመሬት ላይ ያለ ቆሻሻ ማስወገድ

**አካባቢያዊ ፍትህ፡-** ሁሉም የካምብሪጅ ነዋሪዎች በሙሉ ከአካባቢያዊ ተፅዕኖዎች ነፃ እንዲሆኑ ማድረግና ከአካባቢ ሀብቶች በእኩልነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ

## የአየር ንብረትና አካባቢያዊ ግቦችን ለማሳካት ስትራቴጂዎች

1. በከተማዋ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ህንፃዎች ወደተጣራ ዜሮ የካርበን ልቀት የሚደረገውን ሽግግር ማፋጠን
2. ከማጓጓዣ ጋር የተገናኙ የካርበን ልቀትን መቀነስ
3. የካምብሪጅን አረንጓዴ የመሰረተ ልማት አውታርና ዛፍ ጥላ ወደነበረበት እንዲመለስ ማድረግና ማሳደግ እንዲሁም ብዝሃ ህይወትን መደገፍ
4. የድንገተኛ አደጋ ክስተቶች ቁጥጥር ስርዓትንና አሁን ያሉ መሰረተ ልማት አውታሮችን ለአየር ንብረት ለውጥ ውጤቶች ምላሽን እንዲሰጡ ለማድረግ ማዘመን
5. ጠጣር ቆሻሻን ማመንጨትን መቀነስና እንደገና ሊጣራ የሚችልና ኦርጋኒክ ቆሻሻን ከመሬት ወይም ቆሻሻ ማቃጠያ በርሜል በማንሳት እንደገና በጥቅም ላይ ማዋል
6. የአየር፣ የብርሃን፣ የውሃና የድምፅ ብክለትን መቀነስ
7. ለመጠጥ ውሃ ያለ የፍጆታ ጥያቄን መቀነስ
8. የኃይለኛ ዝናብ ውሃ መሰረተ ልማት አውታር ላይ መዋዕለ-ንዋይን በማፍሰስና የጥገና ስራ በማከናወን የኃይለኛ ዝናብ ውሃ መቆጣጠር
9. የከተማዋን የአየር ንብረትና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎችን ለማጠናከር ከአጠቃላይ የካምብሪጅ ማህበረሰብ ጋር መስራት
10. የከተማዋን የአየር ንብረትና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎችንና የፖሊሲ ውሳኔዎችን በአካባቢ ላይ

ሞተር ሆነን በክልላችን የምንጫወተው ሚና እና በክልል እና በዓለምአቀፍ ደረጃ የተቀናጀ ርምጃ መውሰድ ማስፈለጉ ይህንን ተግባር ውስብስብ አድርጎታል፡፡

የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ለህዝብ ማሳወቅ

## ራዕይ 2030

ካምብሪጅ ተፈጥሮአዊ ስርዓቶቿን የምታጎለብት ፣ የካርበን ልቀት መጠንን የምትገድብና

የCambridge ከተማ





## የማህበረሰብ ደህንነት

ማህበረሰብ ማለት ከህንፃዎች፣ ጎዳናዎችና መሰረተ ልማት አውታሮች በላይ ነው- ከቦታ በላይ ነው፡፡ ማህበረሰብ የሚመሰረተው ከአባሎቹ የተለያየ የኋላ ታሪክ፣ ተሞክሮዎች ፣እምነቶች፣ ፍላጎቶች፣ ማንነቶችና ሀብቶች ነው፡፡ ከካምብሪጅ አኳያ ይህ ልዩነት ከተማዋን ለየት ያለ የቦታና የለውጥ ስሜት እንዲኖራት ያደርጋል፡፡ አካታችነትና ማህበራዊ ትስስር ለረጅም ጊዜ ለከተማዋ ግቦች አስፈላጊ ሆኖ የቆየ ቢሆንም በኢኮኖሚው ላይ የቀጠለው ለውጥ ካምብሪጅ እያከበረችው ባለው ልዩነትን (ዳይቨርስቲ) የመገደብ ስጋት ፈጥሯል፡፡ ከታሪክ አንፃር የተገለሉ ነዋሪዎች ለምሳሌ የተለየ መልክ ያላቸው ስደተኞች እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው እንዲሁም መካከለኛ ገቢ የሚያገኙ ነዋሪዎች እየጨመረ ያለ መፈናቀል፣ የቤት እና የፋይናንስ ዋስትና ማጣት እና ከካምብሪጅ የወደፊት መጻዒ እድል እንገለላለን የሚል እያደገ የመጣ ስሜት ያጋጥማቸዋል በተጨማሪም የከተማዋ ነዋሪዎች ስራ እየበዛባቸው ሲሄድ እና የከተማዋ ህዝብ እየተለወጠ ሲመጣ ብዙ ነዋሪዎች በማህበረሰቡ መካከል ያለ ትስስር የመቀነሱ ጉዳይ ያሳስባቸዋል፡፡ ስለዚህ ማህበረሰባችን ደህንነት የተንጠለጠለው ካምብሪጅ ሁሉም ነዋሪዎቿ የሚካተቱ በመሆናቸው ላይ ነው-ነዋሪዎቿ እንቅስቃሴ በሞላባቸው ሰፈሮች ጤናማ ኑሮን መኖር በመቻላቸው፣ ከጎረቤቶቻቸው ጋር ግንኙነት በመፍጠራቸው እና በከተማይቱ የወደፊት እጣፈንታ ድምጻቸውን በማሰማታቸው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

### ግቦች

**እድሎችን ማግኘት፡-** ያለምንም ልዩነት ለሁሉም እድሎችን ማቅረብ፤

**ፍትህ ለሁሉም ሰዎች፡-** በዘር ላይ የተመሰረቱ ልዩነቶችን ማስቆም እና የሁሉንም ዘሮች እኩልነት ማረጋገጥ፤

**የማህበረሰብ ተሳትፎ፡-** ሁሉንም ሰዎች በማህበረሰብ ህይወት ተሳትፎ እንዲያደርጉ አቅማቸውን መገንባት፤

**ጤና እና ደህንነት፡-** ሙሉ ጤናማ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ረጅም እድሜ ነዋሪዎች እንዲኖራቸው የሚያግዙ ሪሶርሶችን እንዲያገኙ ማድረግ፤

**ስነጥበብ እና ባህል፡-** የስነጥበብ መገለጫዎች እና ባህላዊ ወጎቿ በማህበረሰብ ህይወት ውስጥ እንዲሰርጹ የተደረገባት ከተማን ማሳደግ፤

**መማር እና መዝናናት፡-** የህይወት ዘመን ትምህርትን ማበረታታት እና ለጨዋታ እና መዝናኛ እድሎችን ማሳደግ፤

**የባለቤትነት መንፈስ፡-** ማህበራዊ ትስስራችንን ማጠናከር እና ደህንነቱ የተጠበቀ እና ሌሎችን የሚቀበል ማህበረሰብ መፍጠር፤

### የማህበረሰብ ደህንነት ግቦቻችንን ለማሳካት የሚጠቅሙ ስልቶች፡-

1. የዘር እና ባህል ልዩነትን በአካባቢ የፖሊሲ ዝግጅት ላይ ቅድሚያ መስጠት እና ከዘር ጋር በተገናኙ ጉዳዮች ባህላዊ ብቃትን መጨመር፤

4. በተለይም ከታሪክ አንጻር በሚገባ ያልተወከሉ ቡድኖችን ድምጽ እንዲሰጡ እና በመንግስት ውስጥ የተለያዩ ቡድኖች ውክልና እንዲያገኙ ማበረታታት፤

5. ከሚገባው በታች የተወከሉ ቡድኖችን በከተማዋ ፖሊሲ አወጣጥ እና አስተዳደር ያላቸውን ተሳትፎ መጨመር፤

6. በማህበረሰብ ህይወት ውስጥ በቀጥተኛ መርሃ ግብር አወጣጥ እና ለማህበረሰብ ቡድኖች በሚሰጡ ድጋፎች መደበኛና ኢ-መደበኛ ተሳትፎን ማበረታታት

7. የካምብሪጅ ቤተሰቦችን በቅድመ ወሊድ ትምህርት፣ በህጻናት እንክብካቤ አገልግሎቶች እና ቤተሰብን ያማከለ እቅድ ዙሪያ መደገፍ፤

8. ለረጅም ጊዜ አገራቸውን ያገለገሉ እና አካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ነዋሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ማቅረብ፤

9. ቤት አልባነትን ለማስወገድ መስራት እና ቤት ሌላቸውን ነዋሪዎች መጠለያ እና ደጋፊ አገልግሎቶችን በመስጠት መደገፍ፤

10. የሁሉንም የአእምሮ፣ የባህሪ እና ስሜታዊ ጤንነት መደገፍ እና ያልተፈቀዱ ዕጾችን መጠቀምን መቀነስ፤

11. ለሁሉም እድሜ እና ችሎታ ላላቸው ነዋሪዎች ፈጠራ የታከለበት ጨዋታን/መዝናናትን ማበረታታት፤

12. ጤናማ የሆነ የአኗኗር ዘይቤን እና ተመጣጣኝ የምግብ አማራጮችን

## ራዕይ 2030

ካምብሪጅ እያንዳንዱ ሰው ጤናማ፣ በተሳትፎ የተሞላ እና የበለጸገ ህይወትን ለመኖር እድልን የሚያገኝባት ከተማ ናት፡፡ ሰዎች ማህበረሰባቸውን ለመቅረጽ እገዛ መስጠት እንደሚችሉ ያምናሉ፡፡ ከተማዋ በሮቿን ለአዳዲስ መጤዎች እየከፈተች እና የጋራ የወደፊት ዕጣ ፈንታችንን እየተጋራች እያለ ልዩ ታሪኳን እና ተቋሞቿን አክብራ ትይዛለች፡፡

2. ካምብሪጅ የተለያየ ጾታዊ አመለካከት እና የስነጾታ ማንነት ላላቸው ሰዎች የማታሰጋ እና የምታስተናግድ ስፍራ እንድትሆን ማድረግ፤

3. የሃይል ድርጊት ፈጻሚ ባህሪን መገደብ እና የሃይል ድርጊትን አካላዊ እና ስሜታዊ ውጤቶችን እና ለሃይል ድርጊት መጋለጥን ማከም፤

መደገፍ፤

13. የካምብሪጅን ልዩነቶች እና ባህሎች ህጋዊ እውቅና በመስጠት እና በበዓላት አማካኝነት መደገፍ፤

14. የስነጥበብ ባለሙያዎች በካምብሪጅ ውስጥ እንዲሰሩ፣ እንዲገናኙ፣ ስራቸውን እንዲያዘጋጁ፣ እንዲተውኑ እና ስራቸውን እንዲያሳዩ ስፍራ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

15. የስነጥበብ ስራን ተመልካችን በመጨመር ማሳደግ እና ለፕሮፌሽናል እና ፕሮፌሽናል ላልሆኑ የስነጥበብ ባለሙያዎች ድጋፍን መስጠት፤

## ኢኮኖሚ

envisioncambridgema.gov

ካምብሪጅ በወቅቱ በአለምአቀፍ ኢኮኖሚ ተሳትፎ የምታደርግ ከተማ ናት፤ የከተማዋ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች አጠቃላይ ብልጽግናን አምጥተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከተማዋን እንደክልላዊ የኢኮኖሚ ማዕከል ከማምረት በእውቀት ላይ የተመሰረቱ ኢንዱስትሪዎች በመሸጋገር እንድታድግ አግዘዋል፡፡ ቢሆንም ይህን ስኬት ሁሉም አልተጠቀሙበትም፤ ካምብሪጅ በውስጧ የያዘችውን ልዩነት እና የተለዩ የንግድ አውራጃዎቿን መጠበቅ፣ ፍትህ የሰፈነባት ከተማ መሆን እና ለእያንዳንዱ የሚጠቅም ኢኮኖሚን ማሳደግ ትፈልጋለች፤ የካምብሪጅ ልዩነት (ዳይቨርሲቲ) በውስጧ ላለው ንቁ እንቅስቃሴ አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ ይህ ልዩነት ደግሞ ተጠብቆ ሊቀጥል የሚችለው ሁሉም ነዋሪዎቿ የትኛውም የኋላ ታሪክ ቢኖራቸው ጥራት ላለው ስራ፣ የራሳቸውን ንግድ የመጀመር ችሎታ እና የክህሎት ልማት እና ከተማዋ ዋና ዋና ዘርፎቿን፣ ብቅብቅ እያሉ ላሉ ዘርፎቿን እና ቀና ማህበራዊ ውጤትን የሚያመጡ ኢንዱስትሪዎቿን ጠንካራ የስራ አፈጻጸም በንቃት ትደግፋለች፡፡

ነዋሪዎቿ የኑሮ ወጪን፣ የትምህርት ወጪን ለመክፈል የሚያስችሉ መልካም ክፍያ ያላቸው ስራዎችን እና ኢኮኖሚያዊ እድሎችን የሚፈጥሩ አገልግሎቶችን ታቀርባለች፡፡ ሁሉም ነዋሪዎቿ የኋላ ታሪካቸው ወይም ማንነታቸው ከግምት ውስጥ ሳይገባ በካምብሪጅ እድልን ሊያገኙ ይገባል፡፡

### ግቦች

**የጋራ የማህበረሰብ ሃብት፡-** ለስራ እድሎች እና የኑሮ ወጪ መሸፈኛ ገቢ እድል እንዲያገኙ ማድረግ እና እንዲሁም ጠንካራ ትምህርት፣ ስልጠና እና የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረግ፣

**እኩልነት፡-** ከኢኮኖሚያዊ እድል ማጥፋት ማንኛውንም የዘር፣ ስነጾታ እና ሌሎች

### የኢኮኖሚ ግቦቻችንን ለማሳካት የሚጠቅሙ ስልቶች

1. አሁን ያለውን የስልጠናና የትምህርት ፕሮግራም ማሳደግ እና የካምብሪጅ ማህበረሰብን የትምህርት እና የስልጠና ፍላጎት ለማሟላት ከአሰሪዎች እና ከተቋማት ጋር ያለ ሽርክናን ማስፋት፤

2. እኩልነትን፣ የካምብሪጅን የረጅም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነትን እና በውስጧ ያለውን የህይወት ጥራት ለመደገፍ በሚችሉ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ማካተቻ መዋዕለንዋዮችን ማፍሰስ፤

3. ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው የንግድ ቦታን ለመፍጠር እና ለመጠበቅ ማትጊያዎችን መከፈል፤

4. ለአካባቢያዊ፣ ራሳቸውን ለቻሉ

እድገት ለሚያመጡ እድሎችን ማግኘት ሲችሉ ብቻ ነው፤ እቅዱም የተሻለ አካታች የሰራተኛ ገበያን ለመፍጠር ከንግዶች እና ተቋማት ጋር ያለ አጋርነትን ከፍ ለማድረግ እና የከተማዋን ኢኮኖሚያዊ ግቦች ለማሳካት የሚችል አካባቢን በመፍጠር እድገቱን ለመቆጣጠር የመፍትሄ ሃሳቦችን የያዘ ነው፡፡

## ራዕይ 2030

ካምብሪጅ የእውቀት ኢኮኖሚ መሪ አለምአቀፍ ማዕከል እና መልካም ስራዎችን፣ እያደገ ያለ የንግድ አውራጃዎችን እና ከፍተኛ ጥራት ያለውን ህይወት ለሁሉም የምትሰጥ ክልላዊ የኢኮኖሚ ሃይል ማዕከል ናት፤

ልዩነቶችን ማጥፋት፤

**አለምአቀፋዊ የኢኮኖሚ ማዕከል፡-** በአለምአቀፍ የእውቀት ኢኮኖሚ የካምብሪጅን ማዕከላዊነት ማስጠበቅ፤

**ልዩ ልዩ የቅጥር እድሎች፡-** በጥቂት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ካለ ከፍተኛ ክህሎትን ከሚጠይቁ ስራዎች ባሻገር የቅጥር እድሎችን ማብዛት፤

**ልዩ ልዩ ንግዶች፡-** የአካባቢው ንግዶች የተለያዩ አይነቶች፣ መጠኖች እንዲኖሯቸው ማድረግ እና የእድገት ደረጃዎችን በካምብሪጅ ውስጥ እንዲጀምሩ፣ እንዲያድጉ እና እንዲቆዩ ማድረግ፤

**ታላላቅ የንግድ አውራጃዎች፡-** የካምብሪጅን የንግድ አውራጃዎች በተለይም ዋና ዋና አደባባዮቿን እና ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ ኮሪደሮቿን መጠበቅ እና ልዩ ባህሪያቸውን ማሳደግ፤

ንግዶች ቅድሚያ የሚሰጥ እና አካታች ስራ ፈጣሪነትን የሚያጎለብት የንግድ አካባቢ ማበረታታት፤

5. በካምብሪጅ የችርቻሮ አውራጃዎች ንቁ የጎዳና ህይወትን ማበረታታት፤

6. የቀላል ኢንዱስትሪያዊ የመሬት አጠቃቀምን ለመሳተፍ ብዙም አስቸጋሪ ገደብ የሌለባቸውን ስራዎች ለመደገፍ ሲባል መጠበቅ እና ማሳደግ፤

የCambridge ከተማ


OFF



በቦስተን ክልላዊ ከተማ እና በአገሪቱ ውስጥ ለሚኖሩ ብዙ ከተሞች ከፍተኛ የሆነ የመኖሪያ ቤት ጥያቄ አለ፤ ይህ ደግሞ የቤት ዋጋዎችን እንዲጨምሩ ያደረገ ሲሆን ለዝቅተኛ፣ መጠነኛ እንዲያውም ለመካከለኛ ገቢ ቤተሰቦችም ጭምር የማይደፈሩ እየሆኑ ነው፡፡ ተመጣጣኝ ዋጋ ላላቸው ቤቶች በአጠቃላይም ለተጨማሪ ቤት ያለ ፍላጎት በካምብሪጅ ራዕይ የአሰራር ሂደት ባለማቋረጥ ከፍተኛ ትኩረት እና ቅድሚያ እንደሚሰጠው ጉዳይ ተነስቷል፡፡ የከተማዋ ጠንካራ የስራ ገበያ እና ከፍተኛ ጥራት ያለው ህይወት በካምብሪጅ ውስጥ ያለውን የቤት ፍላጎት እንዲጎር በማድረጉ ተከራዮች እና አዳዲስ የቤት ባለቤቶች የሚያወጡትን ወጪ ከፍ አድርጎባቸዋል፡፡ ከተማዋ በቋሚነት ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸውን የቤቶች ቁጥር ለመጨመር እየተገበረቻቸው ያሉ ብዙ ፕሮግራሞች ቢኖሩም እነዚህ ፕሮግራሞች ግን የሪል ስቴት ገበያው የበለጠ ተወዳዳሪ እየሆነ ከመምጣቱ የተነሳ ፈተናዎች እየገጠሟቸው ነው፡፡

## ራዕይ 2030

የካምብሪጅ ነዋሪዎች ለደህንነት አመቺ በሆነ መልኩ፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ባለው እና ህይወትን በሚያረካ ቤት ውስጥ እንዲኖሩ ማድረግ፤ የተለያየ የኋላ ታሪክ ያላቸውን ህዝቦች እዚህ ለመኖር ይመርጣሉ እንዲሁም በማንኛውም ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ እና የህይወት ደረጃ ላሉ የቤት አማራጮች እንዲቀርቡ ማድረግ፣ የሁሉንም የካምብሪጅ ነዋሪዎች የተለያዩ ፍላጎቶችን በተጨማሪም ለተቸገሩ ቀጣይነት ያለው የቤት ድጋፍን ማቅረብ፤ ከተማዋ ቤትን ለማቅረብ በንቃት ትሳተፋለች እንዲሁም ፈጠራ የታከለበት ውጤታማ

## ግቦች

**ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ቤቶች ማዳረስ፡-** ካምብሪጅን የተለያየ ገቢ ያላቸው አባላትን የያዘ ማህበረሰብ ሆና እንድታድግ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ፣ በውል የተገደበ የኪራይ እና የቤት ባለቤትነት እድሎች እንዲኖሩ ማድረግ እና ማስፋፋት፤

**የተለያዩ ቤቶችን ማቅረብ፡-** የተለያዩ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎች፣ የህይወት ደረጃዎች እና ቁሳዊ ፍላጎቶች ላሏቸው ግለሰቦች እና ቤተሰቦች የተለያየ የቤት አማራጭን ማቅረብ፤

**አመቺ ማህበረሰብ፡-** ለጤና አመቺ የሆኑ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ እና ሃይልን ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚጠቀሙ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ቤቶች እንዲኖሩ መደገፍ፤

**የቤት አቅርቦት ዘላቂነት፡-** የካምብሪጅ ነዋሪዎች በካምብሪጅ እንዲቀጥሉ ለማድረግ ያላቸውን ችሎታ መደገፍ ቤተሰቦች ፍላጎታቸውን በተሻለ መልኩ ለማሟላት ወደ ሚመቻቸው ቤቶች እንዲዛወሩ የቤት አማራጮችን እንዲኖሩ ማድረግ፤

**የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ መሆን፡-** በአጠቃላይ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ እንዲሆን መደገፍ እና ክልሉን የቤት ዋጋ ጭማሪን በመቀነስ ረገድ መምራት፤

**እድልን ፈጣሪ ሰፈሮች፡-**

ለህዝብ ማጓጓዣ፣ የስራ ቦታዎች እና

### የቤት ማዳረስ ግቦቻችንን ለማሳካት ስልቶች፡-

1. አጠቃላይ የቤት ምርትን መጨመር
2. ለዝቅተኛ፣ መጠነኛና መካከለኛ ገቢ ቤተሰቦች በቁጥጥር እና የከተማ ዲዛይን የሚያሟሉ እና ተመጣጣኝ ቤቶችን የሚያቀርቡትን ማትጊያ በመስጠት ዋጋቸው ተመጣጣኝ የሆኑ ቤቶችን ማቅረብ፤
3. ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸውን ቤቶች ለመገንባት እና ለመጠበቅ ሚቀርቡ ሃብቶችን መጨመር፤
4. ቤተሰቦች ፍላጎቶቻቸው እየጨመሩ ሲሄዱ በተሻለ መልኩ ወደሚስማማቸው ቤቶች እንዲሻገሩ የሚያስችሉ የቤት አማራጮችን ማቅረብ፤
5. መፈናቀልን እና የቤት ዋስትና ማጣት ችግርን ለመከላከል እና የቤት አጥነትን ችግር መፍትሄ ለመስጠት መሳሪያዎችን እና ሃብቶችን ማብዛት፤
6. የቤት ግንባታን በተለይም በካምብሪጅ እና በዙሪያው ዋጋቸው ተመጣጣኝ የሆኑ ቤቶችን ግንባታ ለመደገፍ በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ መካከል መጠነሰፊ ህብረትን ማጎልበት፤

የቤት ፖሊሲዎችን በማራመድ ክልላዊ መሪ ሆና ታገለግላለች፤

ማህበራዊ አገልግሎቶች ቅርበት ባላቸው የተለያዩ ሰፈሮች ቤትን በማቅረብ እድል ማግኘት የሚችል ማህበረሰብን ማሳደግ፤

## መጓጓዣ

envisioncambridgema.gov

ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝ፣ ቀልጣፋ እና ዘላቂ ማጓጓዣን ማግኘት ለአካታች ኢኮኖሚ፣ የካርቦን ልቀት ቅነሳ፣ የህዝብ ጤናን ለማሻሻል እና በካምብሪጅ ሚኖሩ ነዋሪዎችን የህይወት ጥራት ከፍ ለማድረግ ቁልፍ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ የከተማዋ እንቅስቃሴ (ማጓጓዣ) ፖሊሲዎች ምንም እንኳ በአካባቢው እና በክልሉ ጉልህ የሆነ የህዝብ ቁጥር መጨመር ቢኖርም የቤት መኪናዎችን ቁጥር እድገት ሲገድቡ ቆይተዋል፡፡ በጊዜ ውስጥ የከተማዋ የማጓጓዣ ሲስተሞች ክልሉ እያደገ በመሆኑ የቴክኖሎጂ እመርታዎችን እና የኢኮኖሚ ለውጦችን መላመድ ይኖርባቸዋል፡፡ ካምብሪጅ በአካባቢዋ የሚገኝ የተለያየ የትራንስፖርት ዘዴ (መልቲሞዳል) ትስስርን በማሳደግ፣ ከክልላዊ ዘላቂ ማጓጓዣዎች ጋር ያላትን ግንኙነቶች በማስፋት እና በክልሉ ውስጥ እያደገ ለሚሄድ የማጓጓዣ ፖሊሲ

### ግቦች

**እኩልነት እና ተደራሽነት፡-** የተለያየ እድሜ ችሎታዎች እና ገቢዎች ላሏቸው ሰዎች መጓጓዣ እና እንቅስቃሴ ፍላጎቶችን በተለያዩ የማጓጓዣ አማራጮች ማሟላት፡፡

**አስተማማኝነት እና ቅልጥፍና፡-** ሰዎች እና እቃዎች በካምብሪጅ ውስጥ እና ዙሪያ አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንዲጓጓዙ ማድረግ እና ስፍራ የሚቆጥቡ ማጓጓዣዎች ለምሳሌ በእግር መጓዝ፣ በብስክሌት መጓዝ፣ ከአንዱ የመጓጓዣ ዘዴ ወደ ሌላ የመጓጓዣ ዘዴ መሸጋገር፤ አንድን መኪና ተፈራርቆ መንዳትን ማበረታታት፤

**ደህንነቱ የተጠበቀ እና ንቁ ማጓጓዣ፡-** እንቅስቃሴ የተሞላበት ህይወትን እያበረታታን እና በሁሉም እድሜ ደረጃ ላይ የሚኖሩ እና ችሎታዎች ያሏቸውን ሰዎች ምቾት እያሻሻለ እያለ የትራፊክ አደጋን እና ከፍተኛ ጉዳቶችን የሚያስከትሉ አደጋዎችን

### የእንቅስቃሴ ግቦቻችንን ለማሳካት ስልቶች፡-

1. ለዘላቂ የመጓጓዣ አማራጮች እና ዘላቂነት ያለውን የማጓጓዣ ልማት አውታር በአካል ተደራሽነትን ማሳደግ

2. አሁን ያሉ ዘላቂ መጓጓዣ የመሰረተ ልማት አውታሮችን የበለጠ አመቺ፣ አስተማማኝ እና የማይበገሩ እዲሆኑ ማሳደግ፤

3. ለሁሉም መንገድ ተጠቃሚዎች የደህንነት የመሰረተ ልማት አውታሮችን ማሳደግ እና ማስፋፋት፤

4. አላስፈላጊ የሆኑ የመኪና ጉዞዎችን እና የመኪና ማቆምን ለመገደብ እና ለህዝብ የሚሆን ክፍት ቦታን ለመመደብ የቁጥጥር ማትጊያዎችን እና የመኪና ማቆሚያ ክፍት ቦታዎችን የመሳሰሉ የህዝብ ሃብቶችን ዋጋ ማስተካከል፤

5. ዘላቂ የመጓጓዣ አማራጮችን ለመደገፍ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲን ማስተካከል፤

ድጋፍን በመስጠት ለእነዚህ ተግዳሮቶች ምላሽ መስጠት አለባት፡፡

## ራዕይ 2030

በካምብሪጅ ውስጥ የሚኖር የሚሰራ ትምህርቱን የሚከታተል ወይም የሚዝናና ማንኛውም ሰው ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተመጣጣኝ ዋጋ የሚያስከፍል፣ አመቺ፣ ዘላቂነት ያለው እና ለችግሮች የማይበገር የመጓጓዣ አማራጭ አለው፡፡ በከተማዋ ውስጥ መጓጓዝ በስፍራዎች መካከል ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መዘዋወር ብቻ አይደለም በሂደቱ ለማህበረሰቡ ክፍት ቦታዎችን እና እድሎችን መፍጠርም ጭምር ነው፡፡ የካምብሪጅ የማጓጓዣ እርምጃዎች ፈጠራን የሚያንጸባርቁ እና እኩልነትን የሚያሳድጉ ናቸው፡፡ እንዲሁም ከተማዋ እየተሸሻለ በሚሄድ የማጓጓዣ ፖሊሲ ብሄራዊ መሪ ሆና ትቀጥላለች፤

ማጥፋት፤

**የተገናኘ መሆን እና ለተጠቃሚ ቀላል መሆን፡-** ለመረዳት ቀላል የሆነ፣ የተቀናጀ፣ ቀጣይነት ያለው እና አመቺ የማጓጓዣ ትስስርኔትዎርክን ለሁሉም ሰዎች መፍጠር፤

**የማህበረሰብ ባህሪ እና የዝለቅ አቅም፡-** የከተማዋ የማጓጓዣ ስርዓት የጋራ የማህበረሰብ ክፍት ቦታዎችን የሚደግፍ እና የሰፈሮችን ጎዳናዎች የሚያሳድግ እንዲሆን ማድረግ፡፡

**የአየር ንብረት ለውጥን ተጽእኖን መቀነስ እና የማይበገር መሆን፡-** ከካርበን ነጻ የሆነ የማጓጓዣ ሲስተምን መገንባት እና የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም፤

6. ከየብስ ማጓጓዣ ጋር የተገናኙ መጨናነቆችን ለመቆጣጠር እና ቅልጥፍናና ደህንነትን ለማሻሻል በተሻለ መልኩ የጭነት መጓጓዣን መቆጣጠር፤

7. በካምብሪጅ ውስጥ እና ዙሪያ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቀልጣፋ እንቅስቃሴ ለማድረግ ህዝብ ያለውን መረጃ ማሳደግ እና በማጓጓዣ ደህንነት ላይ የህዝብ ትምህርት ጥረቶችን ማስፋፋት፤

8. በማጓጓዣ ስርአቶች ላይ በቴክኖሎጂ አማካኝነት የሚደርሱ መቋረጦች ለመዘጋጀት አዲስ የቁጥጥር ማዕቀፍን ማስቀመጥ፤

9. በክልሉ በተለይ በካምብሪጅ የተሸከርካሪ ፍሰት ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ባለባቸው አካባቢዎች ዘላቂነት ያለውን የመጓጓዣ መሰረተ ልማት አውታር ለማስፋፋት መስራት፤

የCambridge ከተማ


4117
89.7 WGBH
LOVE





## የከተማ አሠራር ቅርጽ

የህንጻዎች፣ የክፍት ቦታዎች እና የጎዳናዎች ዲዛይን በከተማዋ በሚኖረን ተሞክሮ ላይ ተጽእኖ አላቸው፡፡ ካምብሪጅ ለየት ያለ የዋና ዋና አደባባዮች፣ ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ ግንባታዎች ያሉባቸው አውራጃዎች፣ የንግድ ኮሪደሮች፣ ሰፈሮች፣ ግቢዎች እና ክፍት ቦታዎችን የያዙች ለየት ያለች ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ ተለያዩ የስነህንጻ ዲዛይን ስኬሎች እና ዘይቤዎች ጭምር የሚታዩባት ናት፡፡ ይህ የተለያዩ ነገሮች ድምር ደግሞ ካምብሪጅን ለመኖር፣ ለመስራት ለመማር እና ለመዝናናት አስደሳች እና ደስታን የምትፈጥር ስፍራ ያደርጋታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጠንካራ ኢኮኖሚ ማለት አንዳንድ የከተማዋ አካባቢዎች እንደገና በመልማት ላይ ናቸው ይህ ደግሞ ዋና ዋና አደባባዮችን እና ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ ኮሪደሮችን እንዲሁም በአንድ ወቅት የኢንዱስትሪ አውራጃዎች የነበሩትን የመኖሪያ ሰፈሮችን፣ጠርዞች እና ከመኪና ማቆሚያ ጎን ያሉ አካባቢዎችን ያካትታል፡፡ ካምብሪጅ የማህበረሰብ ጥቅምን ለማምጣት እና የአዳዲስ አውራጃዎች የከተማ ቅርጽ የማህበረሰቡን እሴቶች እንዲጎለብት እና አሁን ላለው ሁኔታ አሚይ እንዲሆን ለማድረግ የእንደገና መልማት እንቅስቃሴን የመጠቀም እድል አላት፡፡

### ራዕይ 2030

በካምብሪጅ ያለው የመንግስት እና የግል ልማት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያለባቸው፣ ጤናማ እና ውብ ስፍራዎችን ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞች፣

### ግቦች

**የልማት ዲዛይን፡-** አሁን ያለውን በሚገባ የተመሰረተ የከተማዋን ዲዛይን መጠበቅ እና የከተማዋን እሴቶች ያለውን በመጠበቅ እና አሚይ ልማቶችን በማከናወን ማሳደግ፤

**እየተለወጡ ያሉ አካባቢዎች እድገት፡-** በአሁኑ ጊዜ በመኪና ማቆሚያ መሬቶች፣ በቤት መኪና አጠቃቀም ላይ የተመሰረቱ እና እድሜያቸው ያረጁ የንግድ ህንጻዎች የሚገለጹ አካባቢዎች ውስጥ ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ፣ በእግረኛ ላይ የተመሰረቱ እና ዘላቂነት ያላቸውን ስራዎች እንደገና የማልማት ተግባር ማከናወን፡፡

**የሽግግር ልማት፡-** በሚገባ በተመሰረቱ አውራጃዎች ጠርዞች ላይ እንደገና የማልማት ስራ ሲከናወን አዲሱ ልማት የቆየውን የጎረቤት ዲስትሪክቶች ዲዛይን የሚያሟላ፣ በአጠቃቀም እና በስፋት ደረጃ ልዩነቶችን የሚያስተናግድ እና በህዝብ ትራንዚት በሚገባ አገልግሎት በሚያገኙ አካባቢዎች የበለጠ ልማትን የሚያካትት ሊሆን ይገባል፡፡

**ክፍት ቦታ፡-** ሁሉንም ነዋሪዎች ከአካባቢው እና ክልላዊ የተፈጥሮሃብቶች ጋር የሚያስተሳስር የተለያዩ ተግባራትን እና ተሞክሮዎችን የሚያቀርብ ሁሉንም ሰዎች የሚያካትት እና ማህበራዊ ትስስርን የሚያበረታታ ከፍተኛ ጥራት ያለውን ክፍት ቦታዎች ትስስር መፍጠር፤

### የከተማ ቅርጽ ግቦችን ለማሳካት ስልቶች፡-

1. የአደባባዮቻችንን እና በኮሪደሮች ያሉ አካባቢዎችን ልዩ ባህሪ እየጠበቅን በመሸጋገሪያ (ትራንዚት) አካባቢዎች ያለውን የልማት መጠን መጨመር፤
2. የካምብሪጅን ሰፈሮች ህንጻዎችን እና የህዝብ መገልገያዎችን ጨምሮ ታሪካዊ ምንነታቸውን እና ልዩነትን (ዳይቨርሲቲ) መጠበቅ፤
3. በአዳዲስ ህንጻዎች በተለይም ለተለያየ ጥቅም በሚውሉ ኮሪደሮች በሚገኙ የምድር ቤት ተግባራትን ማበረታታት፤
4. ለለውጥ ጠንካራ ብቃት ባላቸው አካባቢዎች በስፍራዎች ላይ ያተኮረ እቅድ አወጣጥ እና የልማት ግምገማ ላይ ተመስርቶ ከችግሮች በፊት መፍትሄን ለመስጠት በሚደረግ እንቅስቃሴ ልማቱን መምራት፤
5. ከፍተኛ ጥራት ያለውን ዲዛይን ለመጠቀም ጥረት ከማድረግ ጎን ለጎን የልማት ግምገማ ሂደቱን ለአልሚዎች እና ለህዝቡ የበለጠ ግልጽ እንዲሆን ማሻሻል፤
6. ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የህዝብ መጠቀሚያ ክፍት ቦታዎች ለመፍጠር እና ለማቆየት እንዲሁም ለውጥ አምጪ መርሃ ግብርን ለመቀየስ የግሉን ዘርፍ ልማት መጠቀም፤
7. በአዳዲስ ክፍት ቦታዎች፣ አዳዲስ ፕሮግራሞች እና በተሻሻሉ አካባቢያዊ እና

ተማሪዎች እና ኅብኒዎች ይፈጥራል፡፡ አሁን ላለው ማህበረሰብ እና ለወደፊቱ ትውልዶች ፍላጎቶችን እያሟላን እያለ የከተማዋ ቅርጽ የካምብሪጅን ታሪክ የሚያከብር ነው፡፡

የከተማ ልማት የከተማዋን ባህሪ እና አዳዲስ ነዋሪዎችን እና ተግባራትን በከተማዋ ውስጥ በፍትሃዊ ክፍፍል ለማስተናገድ ማደጓን የሚያመጣጥን ነው፡፡

**አመቺ ማድረግ፡-** በተለይም በህዝብ መገኛ ስፍራዎች እና የንዳና ፊት ለፊቶች አካባቢ ንቁ የህዝብ እንቅስቃሴን ሊደግፍ በሚችልበት አኳያየልማቱን ቅርጽ ጥቅም እና ዲዛይን ቅርጽ ማስያዝ፤

**የዲዛይን ሂደት፡-** ከከተማው የስታፍ አባላት፣ ቦርዶች እና ኮሚሽኖች እና ማህበረሰብ ጋር ባለው ተሳትፎ ግልጽ እና ቀልጣፋ የሆነ የግምገማ የስራ ሂደትን በመፍጠር በሁሉም አዲስ ልማቶች የዲዛይን ልቀትን ለማሳየት መጣር፤

ክልላዊ ግንኙነቶች የህዝብ ክፍት ቦታ ኔትወርክን ማስፋፋት፡፡

8. አሁን ያሉትን ክፍት ቦታዎች የተለያየ ህዝብን እንዲያገለግሉ በመጠበቅ በማደስ እና በማሳደግ የህዝብ ክፍት ስፍራዎች ኔትወርክን ማሻሻል፤

9. ለካምብሪጅ ተቋማት ዩኒቨርሲቲውን እና የሆስፒታል ግቢዎችን ጨምሮ እድገታቸውን አሁን ባሏቸው ግቢዎች ውስጥ እና ጎን ለጎን ባሉ እየተለወጡ ባሉ ለተለያየ አገልግሎት ልማት በሚውሉ አካባቢዎች ላይ እንዲሆን መደገፍ እና ወደ መኖሪያ ሰፈሮች ዘልቀው እንዳይገቡ ማድረግ፤

envisioncambridgema.gov

## ቀጣይ እርምጃዎች

የመጨረሻውን ዕቅድ ህትመት ማውጣት መደበኛው የካምብሪጅ ራዕይ ሂደት ማጠናቀቂያ ይሆናል ነገር ግን ለከተማዋ የተሻለ መጻኢ እድልን የመገንባት ስራ ግን ገና አልተጠናቀቀም፡፡ በዚህ ዕቅድ ላይ የተቀመጡ የመፍትሄ ሃሳቦች ካምብሪጅ እና ብዙ ሌሎች ከተሞች እየገጠሟቸው ያለውን ችግሮች መፍትሔ ለማስገኘት አቅጣጫን ይጠቁማል፡፡ በማህበረሰብ ስብሰባዎች ግልጽ የተደረጉት ራዕይ እና እሴቶች፣ በእነዚህ ገጾች ላይ የተቀመጡ ግቦች እና ስትራቴጂዎች እና ግልጽ የድርጊት ሃሳቦች የፖሊሲ አውጪዎችን፣ የከተማ ስታፍ አባላትን፣ የእቅድ አወጣጥ ቦርድ እና ሌሎች ቦርዶች እና ኮሚሽኖችን አካባቢያዊ እና ዕርዕስታዊ እቅዶችን ሲያወጡ፣ ህግ ሲያወጡ፣ በጀት ሲያዘጋጁ፣ የልማት ምክረሃሳቦችን ሲያጤኑ፣ ለክልላዊ እርምጃ ሲሟገቱ፣ በመጨረሻው እቅድ መሰረት የሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ ክርክር ሊቀርብባቸው እንደሚችል እና በትግበራው ሂደት ወቅት ሊጣሩ እንደሚችሉ እንዲሁም የከተማዋ ለውጥ በሚጠይቀው መሰረት አዳዲስ ሃሳቦችን ጎላ ብለው ሊወጡ እንደሚችሉ ጥርጥር የለንም ይህ በዚህ እንዳለ በኢንቪዥን ካምብሪጅ የተቀመጡ ጠቋሚዎች እና ግቦች የወደፊቱን ፖሊሲ አውጪዎች እና ማህበረሰቡ እነዚህን ውሳኔዎች እንዲወስኑ የሚያግዙ ናቸው፡፡

በሚመጡት አመታት ወደዚህ እቅድ በመመለስ በውስጡ ለተቀመጡት ራዕይ እና እሴቶች-የአጠቃላይ ማህበረሰባችንን እምነቶች እና ግቦች የሚወክሉ ራዕይ እና እሴቶች ስኬት ላይ እንሰራለን፡፡ በየአመቱ በትጋት እና በቁርጠኝነት ለካምብሪጅ ያለን ራዕይ እውን እንዲሆን ሰመስራታችንን እንቀጥላለን፡፡

መሰረተ ልማት አውታርን ዲዛይን ሲያደርጉ፣ ፖሊሲ ሲያወጡ እና
በሌሎችም ጉዳዮች ምሪት ይሰጧቸዋል፡፡

የCambridge ከተማ



# ምስጋና (Acknowledgments)

## የካምብሪጅ ራዕይ አማካሪ ኮሚቴ

## (Envision Cambridge Advisory Committee)

Ruth Allen, Paddy's Lunch
Marlinia Antoine, The Port
Josh Gerber, 1369 Coffee Houset
Frank Gerratana, Cambridgeport
Bill Kane, BioMed Realty Trust
Zeyneb Magavi, Strawberry Hill
Joseph Maguire, Alexandria Real Estate
Risa Mednick, Transition House
Alexandra Offiong, Harvard University
Ebi Poweigha, The Port
Zuleka Queen-Postell, The Port
Ruth Ryals, Neighborhood Nine
Tom Sieniewicz, Planning Board (የዕቅድ ቦርድ
Bethany Stevens, East Cambridge
Tom Stohlman, West Cambridge
Jon Alvarez, MIT
Matthew Wallace, Berry Line
Robert Winters, Mid-Cambridge

## አሌዋይፍ የስራ ቡድን

## (Alewife Working Group)

William Ahern, Alewife Business Association
Doug Brown, West Cambridge
James Butler, Cambridge Self Storage
John DiGiovanni, Trinity Property Management
Mark DiOrio, The Bulfinch Companies
Margaret Drury, North Cambridge
Karen Dumaine, Alewife Transportation Management Association
Margaret Gadon, West Cambridge
Jennifer Gilbert, North Cambridge
Eric Grunebaum, North Cambridge
Catherine Preston Connolly, Planning Board
Tom Ragno, King Street Properties
Sam Stern, West Cambridge
Geoff Wood, North Cambridge

## የአየር ንብረት እና የአካባቢ ስራ ቡድን

## (Climate and Environment Working Group)

Maggie Booz, Strawberry Hill
Maxwell Cohen, North Cambridge
Henrietta Davis, Cambridgeport, የቀድሞ ከንቲባ
Sophia Emperador, North Cambridge
Cynthia Hibbard, Mid-Cambridge
Zeyneb Magavi, Strawberry Hill
Emily Myron, Cambridgeport
Mike Nakagawa, North Cambridge
Julie Newman, MIT
Christopher Nielson, Mid-Cambridge
Steven Nutter, Green Cambridge
Abigail Regitsky, Cambridge Highlands
Julianne Sammut, Neighborhood Nine
Claire Santoro, Agassiz
Joanne Scheuble, East Cambridge
Juliet Stone, Riverside
Henry Vandermark, Neighborhood Nine
Matthew Wallace, Berry Line
Jules Williams, Riverside

## የኢኮኖሚ ስራ ቡድን

## (Economy Working Group)

Chris Barr, Biogen
Tony Brooks, Coast Café
Sarah Gallop, MIT
Josh Gerber, 1369 Coffee House
Theresa Hamacher, Neighborhood Nine
Dave Holtz, Wellington-Harrington
Denise Jillson, Harvard Square Business Association
Jay Kiely, Forest City
Daniel Lander, West Cambridge
Ivy Moylan, Brattle Film Foundation
Gina Plata, Just-A-Start
Ebi Poweigha, The Port
Ruth Ryals, Neighborhood Nine
Daniel Shenfeld, Cambridgeport
Ottavio Siani, Mid-Cambridge
Saul Tannenbaum, Cambridgeport
Mary Ting Hyatt, Bagelsaurus
Ty Wilson, CustomMade

## የተሳትፎ እና የግንኙነት ስራ ቡድን

## (Engagement and Communications Working Group)

የCambridge ከተማ

Debbie Bonilla, Mid-Cambridge
Phyllis Bretholtz, Mid-Cambridge
Justin Crane, North Cambridge
Elaine DeRosa, Cambridge Economic Opportunity Committee (የCambridge የኢኮኖሚ ዕድል ተጠቃሚነት ኮሚቴ)
Tara Greco, Neighborhood Nine
Eryn Johnson, Community Art Center
Justin Kang, City Awake
Sarah Kennedy, Cambridge Chamber of Commerce (የCambridge ንግድ ምክር ቤት)
Ben Peterson, Wellington-Harrington
Zuleka Queen-Postell, The Port
Jeenal Sawla, Mid-Cambridge
Cathie Zusy, Cambridgeport

## የቤት ጉዳይ ስራ ቡድን

## (Housing Working Group)

Leonardi Aray, Strawberry Hill
Mark Boyes-Watson, Cambridgeport
Kelley Brown, MIT
Kathryn Carlson, East Cambridge
Steven Cohen, Mid-Cambridge
Lauren Curry, Just-A-Start
Lee Farris, The Port
Bob Flack, Twining Properties
Anthony Galluccio, Mid-Cambridge, የቀድሞ ከንቲባ እና የስቴቱ ሴናተር
Esther Hanig, The Port
Sean Hope, Hope Legal
Jesse Kanson-Benanav, Wellington-Harrington
Monique King, Cambridgeport
Tom Lorello, Heading Home
Eva Martin Blythe, YWCA
Margaret Moran, የCambridge Housing Authority (የCambridge ቤቶች ባለስልጣን)
Deborah Morse, Agassiz
Cheryl-Ann Pizza-Zeoli, Wellington-Harrington
Zuleka Queen-Postell, The Port
Susan Schlesinger, Cambridgeport
Ellen Shachter, Cambridge and Somerville Legal Services
Robert Winters, Mid-Cambridge

## የመጓጓዣ /ትራንስፖርት/ ስራ ቡድን

## (Mobility Working Group)

Dave Allan, Cambridgeport
Ruth Allen, Neighborhood Nine
Michelle Danila, North Cambridge
Rachel Dias Carlson, Wellington-Harrington
Chris Featherman, Neighborhood Nine
Nate Fillmore, East Cambridge
John Gintell, Mid-Cambridge
Greg Heidelberger, The Port
Mark Jensen, West Cambridge
Caitlin McMurtry, Riverside
Steve Miller, Cambridgeport
Rob Ricchi, Agassiz
Ruthann Rudel, North Cambridge
Emma Sandoe, North Cambridge
Melissa Shakro, MIT
Bethany Stevens, East Cambridge
Stacy Thompson, Livable Streets Alliance
Annie Tuan, Mid-Cambridge
Dustin Weigl, Cambridgeport

## የከተማ የስታፍ አባላት (City Staff)

envisioncambridgema.gov

### የከተማ ልማት መምሪያ (Community Development Department)

Iram Farooq, በማህረሰብ ልማት ረዳት የከተማው ሥራ አስኪያጅ
Melissa Peters, የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ
Cassie Arnaud
Suzannah Bigolin
John Bolduc
Gary Chan
Sandra Clarke
Cliff Cook
Bronwyn Cooke
Chris Cotter
Stuart Dash
Bill Deignan
Christina DiLisio
Seth Federspiel
Stephanie Groll
Lisa Hemmerle
Wendell Joseph
Jennifer Lawrence
Bridget Martin
Khalil Mogassabi
Brendan Monroe
Susanne Rasmussen
Jeff Roberts
Pardis Saffari
Cara Seiderman
Tegin Teich
Erik Thorkildsen

### ገምጋሚ መምሪያ (Assessing Department)

Robert Reardon, ዳይሬክተር

### የካምብሪጅ ጥበባት መማክርት (Cambridge Arts Council)

Jason Weeks, ዋና ዳይሬክተር
Lillian Hsu

### የካምብሪጅ የታሪክ ኮሚሽን (Cambridge Historical Commission)

Charles Sullivan, ዋና ዳይሬክተር

### የህዝብ ስራዎች መምሪያ (Department of Public Works)

### የፋይናንስ መምሪያ (Finance Department)

David Kale, ረዳት የከተማው ሥራ አስኪያጅ
Matthew Nelson

### የሰው ሃይል አገልግሎቶች መምሪያ (Human Services Department)

Ellen Semonoff, ረዳት የከተማው ሥራ አስኪያጅ
Allyson Allen
Shelly Chevalier
Michelle Godfrey
Elizabeth Mengers
Susan Mintz
Emily Singer
Carole Sousa
Sue Walsh

### የፖሊስ መምሪያ (Police Department)

Branville G. Bard, Jr., ኮሚሽነር
Devon Bracher

### የህዝብ ጤና አጠባበቅ መምሪያ (Public Health Department)

Claude-Alix Jacob, ዋና የጤና መኮንን ሃላፊ
Sam Lipson
Kari Sasportas
Kristin Ward
Joséfine Wendel
Anna Wieglosz

### የህዝብ መረጃ ጽ/ቤት (Public Information Office)

Lee Gianetti, ዳይሬክተር

### የትምህርት መምሪያ (School Department)

Dr. Kenneth Salim, ሱፐርኢንቴንደንት
James Maloney
Claire Spinner

### የትራፊክ መኪና ማቆም እና ማጓጓዣ (Traffic, Parking, and Transportation)

Joseph Barr, ዳይሬክተር
Brooke McKenna
Adam Shulman

Owen O'Riordan, ኮሚሽነር
Jerry Friedman
Michael Orr
Kathy Watkins

## የውሃ መምሪያ (Water Department)

Sam Corda, ዳይሬክተር
Frederick Centanni
David Kaplan
Tim MacDonald

ለማህበረሰቡ ተሳታፊ ቡድን ልዩ ምስጋና እናቀርባለን፡፡

የCambridge ከተማ

## አማካሪ ቡድን (ConsultantTeam)

Utile
HR&A Advisors
Interboro Partners
Nelson\Nygaard
Buro Happold
በUniversity of Massachusetts, Boston ውስጥ የሚገኘው የDonahue Institute
McMahon Associates

## የግንኙነት አድራሻ (Contact)

Melissa Peters, AICP
የማህበረሰብ ዕቅድ ዳይሬክተር
Cambridge Community Development Department
(ካምብሪጅ የማህበረሰብ ልማት ክፍል)
344 Broadway
Cambridge, MA 02139
envision@cambridgema.gov
(617) 349-4600
envision.cambridgema.gov

## ስለፎቶዎች ምስጋና (Photo Credits)

ሁሉም ፎቶዎች፣ ታሪካዊ ሰነዶች እና ምስሎች ማስታወሻ ካልተሰጠ በቀር የተከበረው የካምብሪጅ ከተማ ናቸው፡፡ በዚህ ሰነድ ላይ እንደገና እንዲባዙ የተደረጉ ሁሉም ፎቶዎች እና ምስሎች ለቅጂ መብቶች እንዲመረመሩ ተደርገዋል፤ ፣ ፎቶ ወይም ምስል ተለጥፎ ቢገኝ የማውጣት መብት ከቅጂ መብት ባለቤት ስለተገኘ፣ ለህዝብ የተገለጸ መሆኑ ስለሚታወቅ ወይም ግልጽ የቅጂ መብት/የባለቤትነት መብት ስላልተሰጠ ነው፡፡ እያወቁ ቅጂ መብቶችን ወይም አእምሮ ባለንብረት የመሆን መብትን መጣስ በማንኛውም መልኩ የዚህ ሰነድ አላማ አይደለም፡፡ በዚህ ሰነድ ላይ የሚገኝ አንድ ፎቶ ወይም ምስል የቅጂ መብት ባለቤትነቱ በሌሎች የተያዘ መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

Kevin Klein (ገፆች 3, 14, 18)
Molly Akin (ገፆች 17, 21, 22)

Gretchen Ertl (ገፆች 13, 25)
Interboro Partners (ገፆች 4; 8; 9 ከላይ በቀኝ በኩል, በግራ በኩል መሐል ላይ,ከስር በግራ በኩል; 30–31)
Utile (ገፅ 9 ከላይ በግራ በኩል, በቀኝ በኩል መሐል ላይ)

envisioncambridgema.gov


Opportunity
EN
CA
MOBI
Location:
Date: Apr
bike



ENVISION
CAMBRIDGE

